# <u>አላርፍ ያለች ጣት</u>

<u>( ለአፍራሽ  ካድሬዎች አበበ በለውና ምርጫው ስንሻው ምግታር)</u>

ከበደ አራጋው

ራሱ ምግታር የሚለውን ቃል የወሰድኩት ከጋሼ ኃይሉ ገሞራው መሆኑን በቅድሚያ ማሳወቅ እፈልጋለሁ። ለመከራከር ለመገተር፤ ለማቆም በሚለው ትርጉም ውስጇው ነውና የገሞራውን አማርኛ አበላሸቼ ከሆነ በቅድሚያ ይቅርታ። የኢሠፓ ክፉ ካድሬ ሆነው ቆይተው ዛሬ ደግሞ በውስጥ ውስጥ ለወያኔ ያደሩትን በህዝብ ጸርነት ሲሰማሩ በዝምታ ማለፍ የሚለውን አቅዋም በበኩሌ ከቶም አልቀበለውም። ቅጥረኛ ቅጥረኛ መባል አለበት ታጋይ መስሎ ሀገር እንዳያጠፉ።

በመጀመሪያ ግን ጉዳዩን ትኩረት ላልሰጡት ማሳሰብ የምፈልገው አንድ አቢይ ጉዳይ አለ። ካድሬዎቹና ቅጥረኞቹ እንደ አንበጣ የሚፈሉበት የተወሰነ ጊዜና ወቅት አለ። ሩቅ ሳንሄድ ኢዴህጎ (ሕብረት) ሊቋቋም የሁለት ዓመት ጥረት ሲካሄድ የኢሰፓው ካድሬ፤ የመላኩ ተፈራ ምልምል ምርጫው ተብዬ ወስላታ በራዲዮ አማካይነት የደርግ አጫፋሪ የነበሩትን (አሰፋ ጫቦ፤ ሚቼ ረዳት ፕሮፌሰር ዓለም እሸቴን ወዘተ) ጋብዞ በኢሕአፓ ላይ ያካሄደው ቀጣይና ጸያፍ ዘመቻ የሚረሳ አይደለም። ግን አልሆነለትም-- ሕብረትም ተቋቁሞና ከ 15 ያላነሱ ድርጅቶችን አቅፎ ትልቅ አስተዋጽዖ አደረገ። ለወያኔ ቅጥረኛ የሆኑት ባለራዲዮ ካድሬዎች ሕዝብን ለማታለል  ጸረ ወያኔ ሆነው ይቧርቁ ዘንድ ወያኔ ራሷ ታዛቸዋለች። አንዳንድ ራዲዮኖንች ምንም ጸረ ወያኔ ነን ቢሉም በቀጣታ በወያኔ የሚከፈላቸው ለመሆኑ ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አይጠይቅም። ወያኔን የከሰሱ መስሎ ለወያኔ ማደር--ይህ የሰርጎ ገብነት ሀ ሁ ነውና።  በአሁኑ ጊዜ እነዚህ አፍራሽ የወያኔ ካድሬዎች በድርጅቶች ላይ የተነሱበትም ምክንያቱ የባለበት እርገጥ እዛቸው ከወያኔ ተሰጥቷቸው ነው። ለምን አሁን ብሎም መጠየቅ ያስፈልጋል። ወያኔ ሲጨንቀው ካድሬዎቹን ጃስ ይላቸውና በታጋይ ድርጅቶች ላይ ይዘምታሉ። ሕዝብን የጠቀሙ አስመስለው የህዝብ ድርጅቶችን ያደባያሉ። ለወያኔ እሳት ሲመጣበት ውሀ ረጪ የእሳት አደጋ መከላከያ ናቸው።

ለምሳሌ የሰሞኑ የምርጫውና የአበበ  አፍራሽ ሚናና ጸረ ድርጅት ጫጫታ ለምን በተወሰኑ ድርጅቶች ላይ ሆነ? እኔ ድሮ የታገልኩበትና አሁንም የምደግፈው ኢሕአፓን ብንወስድ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ በጣም የተፋፋመ በታታኝ ዘመቻ ተከፍቶበታል። ለምን? በተለይም ስሙን አንጠራም

የለም በተባለ ድርጅት ላይ?! በሀገር ቤት በኣንጃነት የተፈረጀው የሚቹ የጌታቸው ማሩ ፍቅረኛ ነበርኩ ብላ በ እንግሊዝኛ በጻፈቸው መጽሐፍ ተስታከው ለወያኔ ያደሩ የቀድሞ አንጃዎች፤ ተገዢ ምሁራን፤ የደርግ የቀይ ሽብር አራማጆች ሁሉ-- - ማለትም የአብዮቱ ጭንጋፎች ከየቀረና ጉድጓዳቸው ብቅ ብለዋል። የስብሐት ነጋ ቅጥረኛ የሆነ ነጻ ጋዜጠኛ በሉኝ ባይም የዘመቻው ፊታውራሪ ሆኖ በየጋዜጣው ያ ትውልድና ኢሕአፓ ላይ ኡኡ ይላል። በ ውጭ ሀገሮች ደግሞ የወያኔ ምርጥ ካድሬዎች ሳይውሉ ሳያድሩ የዘረኞቹን ጸረ ድርጅት ዘመቻ አጃቢና አስፋፊ ሆነዋል። ዛሬ በወያኔ ላይ ትግሉ እየተፋፈመ ባለበት፤ የሕዝብ እይታ ወደ ጸረ ወያኔው ትግል በዞረበት፤ ሕዝባዊ ትግል ወያኔን ባዋከበት የወያኔና የባዕድ ቅጥረኞች ሌላ የትኩረት አቅጣጫ ከፍተው ሊያደናግሩና በዚያውም ወያኔን ሊታደጉ ላይ ታች እያሉ፤ ይራወጣሉ። ውስጠ ምስጢሩ ለተመልካቾች በጣም ግልጽ ባይሆንም ድርጅቶች የሚጠቁት ባልባሌ ምክንያት መሆኑ ግልጽ ነው። የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን ትግል በጽንፈኝነት ፈርጆ፤ ሽብርተኛውን ወያኔ ትቶ መብቴ ያለውን ዜጋ አሸባሪ ብሎ ክሱና ውንጀላው ተጧጡፋል። ድርጅቶች ለዚህ ሰለባ ናቸው። አበበ በለው እንደ ምርጫው በዚህ ድርጅት ላይ ጸያፍ ዘመቻ የከፈተውም አለምክንያት አይደለም። ማንም አይጠይቀኝም ብሎ ለ ኢሕአፓ መሪ ሰይሞለታል-- የሚያስገርመው ደግሞ በችሎታ ማነስ የተነሳ በድርጅቱ የረባ የአመራር ቦታም ተምድቦ የማያውቀው ግለሰብ "መሪና የአመራር ኮሚቴ ኣባል" ሲባል ዝም ማለቱ ነው። የዛሬ ዓመት ከድርጅቱ በህጉና ደንቡ መሰረት ተባረሩ ወይም ለቀቁ የተባሉትን ግለሰቦች አበበ ለቃለ መጠይቅ ማቅረብ ማንና ምን አስገደደው? ምርጫውስ በዲሲፕሊን ጉድለት የተወገድን የድርጅቱ ወጣት ክንፍ ተወካይ ብሎ ማቅረብ ለምንስ ነበረበት? ይህ ርብርቦሽ በማን የታዘዘ ነው? በሳምንት አራት ሰዓት ራዲዮ የሚጠይቀውንስ ወጪ ማነው የሚከፍለው ? ለምርጫው ጸረ ግንቦት 7 ዘመቻስ ማነው በሀገር ቤት የተደረጉ ንግግሮችን ቅጂ ካሴት አቅራቢ የሆነው ወይስ ግለሰቡ ያኔ ጀምሮ ነቅቶ ንግግሮችን ሲቀዳ ነበር? ለምንስ ይህ ግለሰብ <u>በግል የሚቀርቡበትን</u> ክሶቹን በመጀመሪያ አሌ ብሎ ሊያሳምን አልጣረም? ቀደም ሲል ይኸው ምርጫው ኢሕአፓ በሚያዘጋጃቸው በአሎች ላይ መገኘት ያዘወትር ነበር። ምን አዲስ ክስተት መጥቶ ነው በወያኔው ድርጅት ጸረ ኢሕአፓ እንቅስቃሴ ዋና አዝማች ሊሆን ከአበበ ጋር የተነሳው? አበበ የሚሰራውን የአዲስ አበባ ቤት ተቀማ ወይስ ተደናቀፈበት? ጥያቄዎቹ ብዙ ናቸው--መጠርጠር ሲያንስ ነው ወገኖቼ!

ድርጅቶች ሁሉ የውስጥ ህጋቸውን ማስከበር ግዴታቸው ነው። ህጋቸው ኢዴሞክራሲያዊ ከሆነ አባል አለመሆን ነው። በደጋፊነት የምንቆየው እኮ ድርጅቶች የሚጠይቁት የአባልነት ግደታን መቀበል ስለሚከብደን ነው። አሁን እንደምንሰማው ኢሕአፓ ከአውሮፓ አንድና ከአሜሪካ ጥቂት አባሎችን ሸኝቷል ተብሏል። የሰማነው ምክንያት ምንም ፖለቲካ ይዘት የለውም። ካድሬዎቹም በቃለ መጠይቅ ያስተናገዷቸው ይህ ነው የሚሉት የፖለቲካ ልዩነት ነጥብ ማንሳት አልቻሉም ። አስቂኝ ሆኖ የመጣው ሁለት የኢሕአፓ አመራር አባላት የድርጅት አባል ባልሆኑ ተባረሩ ተብሎ በነ አበበ መናፈሱ ነው ። አባላት በመረጧቸው ላይም የስም ማጥፋት ዘመቻው  በግልጽና ድብቅ ወያኔዎች ተጧጡፏል። ይህ ሁሉ ደግሞ በፈረጠጡት አንጃዎች ተሞክሮ የከሸፈ መስመር ነው ። አባላትንምና የቀሩትን የአመራር አባላት ይንቃል። በአቶ መርሻ የሚመራው የጫጫ አንጃ የዛሬዎቹን ደቀመዝሙሮቹን እያሽኮረመመ መሆኑ ቢታወቅም ቢያንስ የአዛውንቱ የአቶ መርሻ ተከታዮች አለቃቸውን ደግፈው ወያኔን  ተቀብለን (አፊዳቪት ፈርመን) በዘረኞቹ ሸበጥ ስር እንውደቅ ይሉ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ግን ዛሬ ሁለቱ ባለራዲዮ ካድሬዎች ሀይ ሀይ የሚሏቸው ሁሉ ከድርጅቱ ከተባረሩ ወራት አልፈዋል። በዚህ ላይ መግለጫ ባይሰጥም በደጋፊነት እስካወቅነው ድረስ በርካታዎቹ የተሸኙት

1. የድርጅቱን ህግ አክብረው ለረጅም ጊዜ ምንም መዋጮ ባለመክፈላቸውና በ እንቅስቃሴ ባለመሳተፋቸው፤
2. የድርጅቱን የዲሲፕሊን ህግ ጥሰው በሚወገዝ ተግባር ላይ በመሰማራታቸው፤
3. ድርጅቱ የሚቃወመውን ጎጠኝነት በግልጽ በማንጸባረቃቸው፤
4. ከድርጅቱ በስተጀርባ ከጸረ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመጀመራቸው፣ ቡድን በመመስረታቸውና ከሁሉም የከፋው ደግሞ የወያኔን ጸረ ድርጅት ዘመቻን ማጀባቸው ነው። ግለሰቦቹ የሚጽፉት ወይም የሚያሰራጩት (ከድርጅት መዋቅርና አሠራር ውጪ ሆኖ የእርማት እንቅስቃሴ ምን ይባላል!!) አባል ባንሆንም ልከውልናልና ሚናቸውና ጉዳታቸው ላይ ቸልተኛ አይደለንም። ጉዳዩ ግን ምርጫው የደርግ ካድሬና አበበ በለው ኢሰፓ-- ሁለቱም ዛሬ የወያኔ የምስጢር ሰራተኞች ናቸው በእኔ ግምገማ-- ምንኛ ሀገርና ሕዝብን ሊጎዱ ከሌሎች የፖለቲካ መሀይሞችና ተውሳኮች ጋር ገጥመውና አብረው እንደተነሱ ይመሰክራል። የምርጫው የክብር እንግዳ ወያኔው ዳዊት ከበደ ሲሆን ነፍስ ገዳዩ ብርሃኑ ዳምጤ ደግሞ የአበበ በለው ዋና እንግዳ ሆኖ መገኘት ብቻ ሳይሆን በቅርቡ አበበን አጅቦ ለገንዘብ ልመና ላስ ቬጋስ ይሄዳልም ተብሏል ። ጉድ ይሰማ ጆሮ!

ሀቅን መመርመር አለብን ኀበዝ! ዝምታ አይጠቅምምና በነዚህ አፍራሽ የወያኔ ቅጥረኞች ላይ በጋራ መነሳት፤ ማውገዝ፤ ማዕቀብ ማድረግና ከሕዝብ ትግል ሜዳም ማስወጣት ግዳጃችን ሊሆን ይገባል። ታጋይ ድርጅቶች ላይ መዝመት ለወያኔ እንጂ ለማን ይጠቅማል?

ትኩረታችን በጸረ ወያኔው ትግል ላይ ይሁን!

የወያኔ ቅጥረኞች ትግላችንን አይከፋፍሉም !!